# የብልጽግና ፓርቲ የአመራርና የአባላት ዲሲፕሊን መመሪያ

(በብልጽግና ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ የፀደቀ)

ግንቦት 2015 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የብልጽግና ፓርቲ አመራርና የአባላት ዲስፐሊን መመሪያ (ረቂቅ)

ብልፅግና ፓርቲ በኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ብልጽግና ለማረጋገጥ ሁሉንም ኢትዮጵያዊያን አንድ ላይ ያሰባሰበ እና በአገር አቀፍ ፓርቲነት በሕግ አግባብ ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ የፖለቲካ ፓርቲ በመሆኑ፤

በጥብቅ የፓርቲ ሥነ-ምግባር የሚመራ አመራር እና አባል የፓርቲውን ፕሮግራምና እቅዶች በስኬታማነት ለመፈፀምና ለማስፈፀም አስፈላጊ በመሆኑ፤

የፓርቲ አመራሮች እና አባላት በጥብቅ ሥነ-ምግባር እንዲመሩ ማድረግ የፓርቲውን ውስጣዊ ጥንካሬ፣ ዲሲፕሊንና አንድነት የሚያጎለብትና ሕዝባዊ ቅቡልነቱን የሚጨምር በመሆኑ፤

የፓርቲው አባላት ሊከተሏቸው የሚገቡ የሥነ-ምግባር መርሆዎች፣ ግዴታዎች እና በሥነ-ምግባር ጥሰት የሚወሰዱ እርምጃዎች የሚመራበት ግልጽ የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 13(1) (በ) እና 23(6) (ረ) መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የብልጽግና ፓርቲ የአመራርና የአባላት ዲሲፕሊን መመሪያ ቁጥር ……/2015" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

1) **"ፓርቲ"** ማለት የብልጽግና ፓርቲ (ብልጽግና) ነው፡፡
2) **"መተዳደሪያ-ደንብ"** ማለት የብልጽግና ፓርቲ በአንደኛው መደበኛ ጉባኤው ያፀደቀው የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ማለት ነው፣
3) **"ጉባኤ"** ማለት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የብልጽግና ፓርቲ ከፍተኛ የአመራር አካል ነው፤
4) **"ማዕከላዊ ኮሚቴ"** ማለት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ከጉባኤ እስከ ጉባኤ ፓርቲውን የሚመራ ከፍተኛ የብልጽግና ፓርቲ አካል ነው፤

5) **"ኮሚሽን"** ማለት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በየደረጃው የተቋቋመው የፓርቲው የኢንስፔክሽንና የሥነ-ምግባር ኮሚሽን ማለት ነው፤

6) **"ዋና ጽ/ቤት"** ማለት በብለጽግና ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 24 መሰረት የተቋቋመ የብልፅግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ነው፡፡

7) **"ቅርንጫፍ ጽ/ቤት"** ማለት በብልፅግና ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 25 እና አንቀጽ 6 መሰረት የተቋቋሙ ከክልል/የከተማ አስተዳደር ጀምሮ እስከ ቀበሌ ባሉ መዋቅሮች የተቋቋመ የብልፅግና ፓርቲ ቅ/ጽ/ቤት ማለት ነው፡፡

8) **"መመሪያ"** ማለት የብልጽግና ፓርቲ የሥነ-ምግባር እና የዲስፕሊን እርምጃ አወሳሰድ መመሪያ ነው፡፡

9) **"መልካም የፓርቲ ሥነ-ምግባር"** ማለት በመተዳደሪያ ደንቡ ውስጥ የተደነገጉ የአባልነት ግዴታ፣ የፓርቲው መርሆዎች፣ እሴቶችና የአሰራር መርሆዎችንና የፓርቲውን ስነ-ምግባር ማክበርና በጥብቅ መፈፀም እንዲሁም ህብረተሰቡ የሚስማማባቸውን የግብረ-ገብ እሴቶችን ማክበርና መልካም ተግባራትን በመፈጸም አርአያ ሆኖ መገኘት ማለት ነው፡፡

10) **"የሥነ-ምግባር ጥፋት"** ማለት በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብና የተለያዩ የአሰራር መመሪያዎች ውስጥ የተጠቀሱትን የፓርቲው መርሆዎች፣ እሴቶችና የአሰራር መርሆዎች እና ህብረተሰቡ የሚስማማባቸው የግብረ-ገብ እሴቶችን የሚቃረን ድርጊት ፈጽሞ መገኘት ነው፡፡

11) **"የፖለቲካ ጥራት"** ማለት ፓርቲው የሚመራበት የመደመር እሳቤ እና የፖለቲካ ፕሮግራም ላይ የፀና አቋም ያለው፣ የአመለካከት ጥራትና የአስላለፍ ግልጽነት ያለው፣ በኢትዮጵያ የሕዝቦች፣ የብሔር፣ የእምነት፣ የጾታ፣ የአኗኗር ዘይቤና የአስተሳሰብ ልዩነት እውነታ መሆኑን ተቀብሎ ለሕብረብሔራዊ አንድነት፣ እኩልነትና የጋራ ግብ የሚተጋ፣ የሕዝቡን ህይወት ለመለወጥና ጠንካራ ተቋማዊ ስርዓት ለመገንባት በቁርጠኝነት የሚሰራ እንዲሁም የፓርቲውን ዓላማ ከሚያደናቅፉ ፅንፈኝነት፣ አክራርነትና ልግመኝነት በአመለካከትና በተግባር ነጻ በመሆን የፓርቲን ተልዕኮ በብቃት መፈፀም ማለት ነው፤

12) **"ሙስና"** ማለት ህግና ስርዓትን ተከትሎ ከመስራት ይልቅ ስልጣንና ኃላፊነትን ያለአግባብ በመጠቀምና ህግና ስርዓትን በመጣስ የመንግስትና የህዝብ ሀብትና ንብረትን መስረቅ፣ መዝረፍ፣ ማጭበርበር፣ እንዲሁም በጉቦ፣ በዝምድና፣ በትውውቅ፣

በጎሰኝነት፣ በፖለቲካ ወገኝተኝነት እና በኃይማኖት ትስስር በመመርኮዝ ፍትህን እያዛቡ የግል ጥቅምን ማካበትና ሌላውን ወገን ተገቢ ባልሆነ መንገድ መጥቀም ወይም መጉዳት ነው፤

13) **"መርህ አልባ ግንኙነት"** ማለት የመንግስት ወይም የፓርቲ መርሆዎችን በተፃረረ መልኩ የግል ጥቅምና ፍላጎትን ለሚሟላት ሲባል ከባለሀብቱ ወይም ከሌሎች አካላት ጋር የሚፈጠር ግንኙነት ማለት ነው፤

14) **"ያልተገባ የጥቅም ትስስር"** ማለት የተሰጠውን ኃላፊነት ተጠቅሞ ያልተገባ ትስስር በመፍጠር ባልተገባ መንገድ ሀብት ለማፍራት ተፅዕኖ ፈጥሮ ጉዳዮችን ከህግና አሰራር ውጭ እንዲፈጸሙ ማድረግ ማለት ነው፤

15) **"ሙስናን መዋጋት"** ማለት የፓርቲ አባላት፣ አመራርና አካላት የአገሪቱን የፀረ-ሙስና ህግ የማክበር፣ የማስከበር፣ የፓርቲውንና የመንግስትን ንብረትና ሀብት በአግባቡ መያዝን፣ ከሌብነት፣ ብልሹ አሠራርና አድሏዊ ድርጊቶች መራቅ፣ ሌብነትንና ሙስናን መጠየፍ፣ ሙሰኞችን መታገል፣ ያልተገባ ጥቅም አለመፈለግ፣ በሙስና አስከፊነት ላይ በቀጣይነት ግንዛቤ መፍጠር እና ለሙስና በር የሚከፍቱ ቀዳዳዎችን ለይቶ መዝጋት ማለት ነው፡፡

16) **"መረጃ"** ማለት የፓርቲው ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎች፣ እቅዶች፣ ሪፖርቶች፣ ቃለ ጉባዔዎች፣ ውሳኔዎች፣ የአባላት ፕሮፋይል፣ እንዲሁም በተለያየ ጊዜ ለፓርቲው ስራዎች እንዲያገለግሉ የታተሙና ያልታተሙ የፓርቲው ሠነዶች ማለት ነው፡፡

17) **"ፅንፈኝነት እና አክራሪነት"** ማለት ሃይማኖትን፣ የብሔር ብሔረሰቦችንና ሕዝቦችን መብትንና ሌሎች ጉዳዮችን በተመለከተ ፓርቲው ከሚያራምደው የመሃል ፖለቲካ በተቃራኒ ዋልታ ረገጥ የሆነና ሃይማኖት፤ ብሄርንና ሌሎች ማንነቶችን ሽፋን በማድረግ ማህበራዊ ትስስርን የመበጣጠስ ውጤት ያለው ተግባር/ምግባር ነው፡፡

18) **"አባል"** ማለት የፓርቲውን ፕሮግራም ተቀብሎ በመተዳደርያ ደንቡ መሰረት የፓርቲ ሙሉ አባል ወይም እጩ አባል የሆነ ማለት ነው፡፡

19) **"አመራር"** ማለት የፓርቲውን ፕሮግራም ለማስፈጸም በየደረጃው ባለው የፓርቲው መዋቅሮች በሃላፊነት የተመደበ ወይም የተመረጠ ማለት ነው፡፡

20) **"የአደረጃጀት ዘርፍ"** ማለት በየደረጃው ባሉ የፓርቲ ጽ/ቤቶች የተደራጁና የአመራሮችና የአባላት ምልመላ፣ ምደባ፣ ሹመት እና የአደረጃጀቶች እንቅስቃሴ

በአደረጃጀትና አሰራር መመሪያው መሰረት መሆኑን የመከታተል፣ የመደገፍ እና መረጃዎችን አደራጅቶ በአግባቡ የመያዝ ኃላፊነት የተሰጣቸው አካላት ማለት ነው፡፡

21) በመመሪያው በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትን ፆታም ይመለከታል፣

## 3. ዓላማ

1) የብልጽግና ፓርቲ አመራርና አባላት በመልካም የፓርቲ ስነ ምግባር በመመራት የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ፣ መመሪያዎች እና እቅዶች በውጤታማነት ተግባራዊ እንዲያደርጉ ለማስቻል፣
2) ፓርቲው ኢትዮጵያ ያላትን እምቅ አቅምና እድል በሚገባ በመጠቀም ፕሮግራሙንና እቅዶቹን በብቃት ለማስፈፀም የሚያስችለውን የአመራሮችና የአባላት የፖለቲካ ጥራት፣ የውስጠ ፓርቲ ዴሞክራሲ ጥንካሬ እና የውስጠ ፓርቲ አንድነት እንዲኖረው ለማስቻል፣
3) የሥነ-ምግባር ጥሰት የፈፀሙ የብልጽግና አመራሮችና አባላት ላይ የእርምት እርምጃ የሚወሰድበትን ግልጽ የአሰራር ሥርዓት ለመዘርጋት እና
4) ብልጽግና ፓርቲ በአመለካከቱም በተግባሩም በጥሩ ምሳሌነት የሚጠቀስ አባልና አመራር ያለው ፓርቲ መሆኑን በማረጋገጥ የተጽእኖ አቅሙንና ሕዝባዊ ቅቡልነቱን ለማሳደግ ይሆናል፡፡

## 4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በየደረጃው በሚገኘው የፓርቲ መዋቅር፣ አመራርና አባላት ላይ ሁሉ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

# ክፍል ሁለት

## የአባላት ሥነ-ምግባር መርሆዎች እና ግዴታዎች

### 5. መርሆዎች

የስነ ምግባር መመሪያዉ በሚከተሉት መርሆዎች ይመራል፡፡

1) እውነተኛነት፣
2) የሕዝቦችና የፓርቲው የወል እውነት፣
3) ዴሞክራሲያዊነት፣
4) የውስጠ ፓርቲ አንድነት፣
5) የህግ የበላይነት፣
6) ተጠያቂነት፣
7) ሚዛናዊነት፣

### 6. የአመራርና አባላት የሥነ-ምግባር ግዴታዎች

1. ማንኛውም የፓርቲው አመራርና አባል ህጎችንና አሰራሮችን የማክበር የሥነ-ምግባር ድንጋጌዎችን የማክበር ግዴታ ይኖርበታል፡፡

   ሀ) የፓርቲውን ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ እና የአሰራር መመሪያዎችን የማክበርና ለተግባራዊነታቸው በግንባር ቀደምትነት የመታገል፣

   ለ) የፓርቲውን መርሆዎች፣ እሴቶችንና የስነ-ምግባር ህግጋትን የማክበር፣ የህዝቡንና የሀገርን ደህንነትና ሉአላዊነትን የመጠበቅ፣

   ሐ) በፓርቲው ህጋዊ አሰራር መሰረት በየደረጃው በሚገኙ የፓርቲው አደረጃጀቶች የሚወሰኑ ውሳኔዎችን የማክበርና የመፈጸም፣

   መ) የሀገሪቱን ህጎችንና መንግስታዊ ውሳኔዎችን በማክበርና በማስከበር አርአያ ሆኖ የመገኘት፣

   ሠ) የህግ የበላይነትን በማክበርና በማስከበር ግንባር ቀደም ሚና የመወጣት፣

   ረ) የህብረተሰቡን መልካም እሴቶች የማክበርና በህብረተሰቡ ዘንድ እንደ መጥፎ ስነ-ምግባር ከሚቆጠሩ የስነ-ምግባር ድርጊቶች እራስን የመቆጠብ፣

2. ማንኛውም የፓርቲው አመራርና አባል የውስጠ ፓርቲ ዴሞክራሲን የማጠናከርና ከገዳቢ ድርጊቶች የመቆጠብ የሥነ-ምግባር ድንጋጌዎችን የማክበር ግዴታ ይኖርበታል፡፡

ሀ) በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብና የአሰራር መመሪያዎች መሰረት ለአባላት የተሰጡ መብቶች በተሟላ ሁኔታ የማክበርና የማስከበር፣

ለ) በፓርቲው ውስጥ አባላት ሉዓላዊ የስልጣን ባለቤት በመሆናቸው በፓርቲው ህጎችና አሰራሮች መሰረት በማንኛውም የፓርቲ ስራዎችና እንቅስቃሴዎች የአባላትን ተሳትፎ የማረጋገጥ፣

ሐ) የአባላትን በህጋዊ መንገድ በየደረጃው ባሉ የፓርቲ መዋቅሮች ሃሳባቸውን በቃልም ሆነ በጽሁፍ የማቅረብ መብታቸውን የማክበር፣

መ) አባላት ስለፓርቲው ማወቅ የሚገባቸውን ጉዳይ እስከ ፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ድረስ የመጠየቅና መልስ የማግኘት መብታቸውን የማክበር፣

ሠ) የፓርቲውን ዶክመንቶች ለአባላት ተደራሽ በማድረግ ምቹ ሁኔታ የመፍጠር፣

ረ) በፓርቲው ውስጥ አሳታፊና ግልጽ ውይይትና የክርክር መድረኮችን ቀጣይነት ባለው ሁኔታ በመፍጠር በፓርቲው ውስጥ የሃሳብና የተግባር አንድነት እንዲጎለብት የበኩሉን ድርሻ የመወጣት፣

ሰ) የእርስ በእርስ ግንኙነቶች በመተባበር፣ በመከባበርና በመቻቻል ላይ የተመሰረቱ እንዲሆኑና የሚያጋጥሙ ልዩነቶችና ግጭቶች በውይይትና በዴሞክራሲያዊ ትግል እንዲፈቱ በማድረግ የሚጠበቅትን ኃላፊነት የመወጣት፣

ሸ) አባላት ሂስ በማቅረባቸው፣ ያልተገባ ድርጊትን በመታገላቸውና በመሰል ሁኔታዎች በመመስረት የቂም በቀል ድርጊት ከመፈጸም እራስን የመጠበቅና በዚህ ሁኔታ ያልተገባ ድርጊት የሚፈጽሙትን የመታገል፡፡

3. ማንኛውም የፓርቲው አመራርና አባል የፓርቲውን ውስጣዊ አንድነት፣ ጥራትና ጥንካሬ የመጠበቅ የሥነ-ምግባር ድንጋጌዎችን የማክበር ግዴታ ይኖርበታል፡፡

ሀ) የፓርቲውን የፖለቲካ እሳቤዎች በብቃት የመገንዘብ፣ ለሌሎች የማስገንዘብና የተዛቡ አመለካከቶችን በዴሞክራሲያዊ መንገድ የመታገል፣

ለ) የፓርቲውን ውስጣዊ አንድነት፣ ጥራትና ጥንካሬ የሚጎዱ ማናቸውንም ዝንባሌዎችና ድርጊቶችን የማጋለጥና የመታገል፣

ሐ) በፓርቲው ውስጥ በአባላት መካከል የሚኖርን መልካም ግንኙነት ከሚያጎድፉ ድርጊቶች የመቆጠብ፣

መ) የራስን ድክመት በቅንነት የማረምና የሌሎች ድክመት እንዲታረም በዴሞክራሲያዊ መንገድ የመታገል፣

ሠ) ያለውን እውቀትና ክህሎት ለሌሎች የማስተላለፍና ከሌሎች ለመማር ዝግጁ የመሆን፣

ረ) ስራንና ተግባርን ማእከል ያደረገ ወቅቱን የጠበቀ ግምገማ እና ምዘና በማካሄድ ጥንካሬዎችን አጠናክሮ በማስቀጠልና ድክመቶችን በማረም ቀጣይነት ላለው ስኬትና ለውጥ በትጋት የመስራት፣

ሰ) ፓርቲው ውስጥ ቡድንተኝነትና አንጃነትን በመፍጠር የፓርቲውን አንድነት ከሚጎዱ ድርጊቶች እራስን የመጠበቅና ሌሎችን የመታገል፣

ሸ) የፓርቲውን የፋይናንስ አቅም ለማጠናከር የፓርቲ አባልነት መዋጮ በወቅቱ የመክፈል፣

4. ማንኛውም የፓርቲው አመራርና አባል የፓርቲውን እና የመንግስት ሚስጥር ስለመጠበቅ የሥነ-ምግባር ድንጋጌዎችን የማክበር ግዴታ ይኖርበታል፡፡

ሀ) የፓርቲውንና የመንግስት ሚስጥራዊ ሰነዶች፣ ዶክመንቶች እንዲሁም ለሌሎች አካላት ተላልፈው መሰጠት የለባቸውም የተባሉ ጉዳዮችን በአግባቡ የመያዝ ግዴታ ይኖርበታል፤

ለ) በተለያዩ ውይይቶችና ስብሰባዎች የሚተላለፉ ውሳኔዎችን ከሚመለከተው አካል ውጭ ለሌላ አካል ማሳወቅ አይቻልም፤

ሐ) የማንኛውንም አባልም ሆነ አካል በሚስጥር መያዝ አለባቸው የተባሉ ጉዳዮችን ወደ ውጭ ማውጣት የተከለከለ ነው፡፡

5. ማንኛውም የፓርቲው አመራርና አባል ሙስና፣ ብልሹና አድሏዊ አሰራሮችን የመታገልና የሥነ-ምግባር ድንጋጌዎችን የማክበር ግዴታ ይኖርበታል፡፡

ሀ) የፓርቲና የመንግስት ገንዘብና ንብረት የመጠበቅና ለእራስ ጥቅም ያለማዋል፣

ለ) በተሰማራበት የፓርቲና የመንግስት ስራና ኃላፊነት እራስን ከሙስናና ከብልሹ አሰራሮችና ድርጊቶች የመጠበቅና ሌሎችን የመታገል፣

ሐ) በተሰማራበት የፓርቲና የመንግስት ስራና ኃላፊነት ብሄርን፣ ሃይማኖትን፣ ጾታን ወይም መሰል ሁኔታን መሰረት በማድረግ አድሏዊ አገልግሎቶችና ውሳኔዎች ከመስጠት እራስን የመጠበቅና ሌሎችን የመታገል፣

መ) የሃሰት ሪፖርት ያለማቅረብና የቀረቡለትን ሪፖርቶች ትክክለኛነት የመከታተልና የማረጋገጥ፣

ሠ) በሃሰተኛ መረጃ በመመስረት ቅሬታና አቤቱታ ያለማቅረብ እና ሌሎችን በሃሰት ያለመወንጀል፣

ረ) የፓርቲ ሚስጥሮችን ከፓርቲው አሰራር ውጭ በማንኛውም መንገድ አሳልፎ ከመስጠት እራስን የመጠበቅና ሌሎችን የመታገል፣

ሰ) ትክክለኛ ባልሆነ መረጃ በመመስረት የፓርቲ አባላት ምልመላ ከማካሄድ እና ህግና አሰራርን ሳይከተል የአባልና የአመራር ምደባና ስምሪት ከመስጠት እራስን የመጠበቅና ሌሎችን የመታገል፣

6. ማንኛውም የፓርቲው አመራርና አባል ፓርቲውን ሳይለቅ የሌላ የፖለቲካ ፓርቲ አባል መሆን ክልክል መሆኑን የሚመለከቱ የሥነ-ምግባር ድንጋጌዎችን የማክበር ግዴታ ይኖርበታል፡፡

ሀ) የብልጽግና ፓርቲ አባል የሆነ ሰው በብልጽግና ፓርቲ አባልነት እያለ የሌላ ፓለቲካ ፓርቲ አባል መሆን አይችልም፤

ለ) ከፓርቲያችን አቋሞች ጋር በሚፃረር መልኩ የሌሎች ፖለቲካ ፓርቲዎችን አቋም የማራመድም ሆነ የመደገፍ አዝማሚያዎችን ካሳዬ በሥነ-ምግባር ጥሰት ተጠያቂ ይደረጋል፣

# ክፍል ሶስት

## የሥነ-ምግባር የግንኙነት አግባቦች

### 7. በፓርቲው አባላትና አመራር መካከል ሊኖር የሚገባ ግንኙነት፣

በማንኛውም የፓርቲ አመራርና አባላት መካከል የሚኖር ግንኙነትን በተመለከተ አመራሩና አባሉ የሚከተሉትን የስነ-ምግባር ድንጋጌዎችን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

1) እያንዳንዱ የብልጽግና ፓርቲ አባል የሰው ልጅ ሁሉ እኩል መሆኑን ተቀብሎ ለተግባራዊነቱ መስራት ይጠበቅበታል፤
2) እያንዳንዱ የብልጽግና ፓርቲ አባል ለሌላው በወንድማማችነትና እህትማማችነት እሴት ላይ የተመሰረተ አክብሮት ሊኖረው ይገባል፤
3) እያንዳንዱ አባል ከሌላው የፓርቲው አባል በግልጽ መነጋገርን፣ መረዳዳትን፣ መማማርን፣ መደጋገፍን፣ መተባበርን፣ መተማመን፣ መከባበርንና መርህን በጠበቀ መልኩ ለፓርቲው ዓላማ በጋራ መሰለፍን ማዕከል ያደረገ ግንኙነት ሊኖረው ይገባል፤
4) እያንዳንዱ አመራር ሰልጣንን አላግባብ በመጠቀም በሌላው የፓርቲ አመራርና አባል ላይ የግል ፍላጎትን መሰረት ያደረገ ጫና ከመፍጠር መቆጠብ ይኖርበታል፤
5) የኢትዮጵያዊ ባህሎችና እሴቶች በሚያዙት መሰረት ማህበራዊ ትስስሮችን መፍጠር ይኖርበታል፤
6) ከሀሜት፣ አሉባልታና በጥርጣሬ ላይ ተመስርቶ ስም ከማጥፋት መቆጠብ ይኖርበታል፤
7) ከፓርቲው አሰራር በተቃረነ መልኩ ተሰማርቶ የተገኘ የብልጽግና ፓርቲ አባልም ሆነ አመራር እንዲታረም የማድረግ ሃላፊነት ይኖረዋል፡፡

### 8. በመንግስት ስራ ላይ ስለሚኖር ግንኙነት

ማንኛውም የፓርቲ አመራርና አባል በመንግስት ስራ ሊኖረው የሚገባ ግንኙነት በተመለከተ የሚከተሉትን የስነ-ምግባር ድንጋጌዎችን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

1) ብልጽግና ገዥ ፓርቲ በሚሆንበት ወቅት የፓርቲው አመራር በሚመራበት የመንግስት መስሪያ ቤት ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎችንና እቅዶችን ከፓርቲያችን ፕሮግራም ጋር በተጣጣመ መልኩ በግንባር ቀደምትነት በውጤታማነት የመፈጸምና የማስፈፀም ግዴታ አለበት፤

2) የመንግስት ተቋማት ነፃ፣ ገለልተኛ እና ሙያዊ ብቃት ያላቸው እንዲሆኑ በትጋት የመስራት ግዴታ አለበት፤
3) የተቋም ግንባታን በሚጎዳና ከመርህ ውጭ በሆነ አግባብ የመንግስት እና የፓርቲ አሰራሮች መደበላለቅ የማስወገድ ኃላፊነት አለበት፤
4) የመንግስትን ስራ የሚመሩ አመራሮች እርስ በርስ የመተጋገዝ፣ የመተባበር እና ልምድ በመለዋወጥ ብቃት የማሳደግ ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፤
5) የፓርቲ አባላት የሆኑ የመንግስት ሠራተኞች ከአመራሩ ጋር ለጋራ ዓላማ በትብብር የመስራት እና የፓርቲውን መርሆዎችና እሴቶች በመላበስ የመንግስት ሥራቸውን በግንባር ቀደምትነት የመፈፀም ግዴታ አለባቸው፤
6) የፓርቲው አመራሮችና አባላት ካለ በቂ አሳማኝ ምክንያት ከሥራ መቅረትም ሆነ ማርፈድ እንዲሁም ተጠሪ ከሆኑለት አካል ወይም የግድ መገኘት ባለባቸው መድረክ ከአዘጋጁ አካል ፍቃድ ሳያገኙ መቅረትም ሆነ ማርፈድ ተጠያቂ ያደርጋል፡፡

## 9. ከህዝብ እና ከሲቪል ማህበራት ጋር የሚኖረው ግንኙነት፣

ማንኛውም የፓርቲ አመራርና አባል ከህዝብ እና ከሲቪል ማህበራት ጋር የሚኖረው ግንኙነትን በተመለከተ የሚከተሉትን የስነ-ምግባር ድንጋጌዎችን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

1) በኢትዮጵያ ለሚደረገው የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ብልጽግና እውን መሆን ህዝብ ወሳኝ አካል መሆኑን በማመን ህዝቡን በዕቅዶቻችንና በአፈጻጸሞቻችን ላይ ግልጽነት ባለው መልኩ ማሳተፍ፤
2) የልማት ስራዎቻችን ሰው ተኮር መሆናቸውን በተግባር ማረጋገጥ፤
3) ለዴሞክራሲ ባህል መዳበርና ለፖለቲካዊ ብልጽግና መረጋገጥ ሲቪል ማህበራት ሚናቸው የጎላ መሆኑን በመገንዘብ አስፈላጊውን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
4) በየደረጃው የሚገኘው የብልጽግና አባልና አመራር መርህ በጠበቀ አኳኃን ከሲቪል ማህበራት ጋር ተቀራርቦ የመስራት፣ በማህበራዊና ኢኮኖሚ ልማት ሥራዎች የማሳተፍ እና ህግና ሥርዓትን አክብረው እንዲሰሩ የማድረግ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## 10. ከግል ዘርፍ/ባለሀብት ጋር ሊኖር የሚገባ ግንኙነት፣

ማንኛውም የፓርቲ አመራርና አባል/ላት ከግል ዘርፍ/ባለሀብት ጋር የሚኖር ግንኙነትን በተመለከተ የሚከተሉትን የስነ-ምግባር ድንጋጌዎችን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

1) የግል ዘርፉ በኢኮኖሚ እድገት ውስጥ የሚኖረውን ሚና(ዋናኛ ተዋናይ መሆኑን) የመረዳትና ለተግባራዊነቱ መርህን በጠበቀ መልኩ የድርሻውን የመወጣት ኃላፊነት አለበት፤
2) የግል ዘርፉ ጤናማና ተወዳዳሪ እንዲሆን ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለው አሰራር የመደገፍ እና ምቹ ሁኔታ የመፍጠር ኃላፊነት አለበት፤
3) ከባለሀብቱ ጋር የሚኖረን ተግባቦት በተነፃፃሪ ነፃ፣ ገለልተኛና መርህን መሰረት ያደረገ ሊሆን ይገባል፤
4) በማንኛውም መልኩ ከባለሀብቶች ጋር ያልተገባ የግል ጥቅም ትስስር መፍጠር ፈጽሞ የተከለከለ ነው፤
5) ከማንኛውም የግል ዘርፉን አዎንታዊ ሀገራዊ አስተዋጽኦና እንቅስቃሴ ከሚገድቡ አመለካከትና ተግባራት የመቆጠብ ግዴታ ይኖርበታል፤
6) አባሉ እራሱ ባለሀብት በሚሆንበት ወቅት ህግና ሥርዓትን በማክበርና ለሀገር ብልጽግና አዎንታዊ አስተዋጽኦ በማበርከት ረገድ ግንባር ቀደምና አርዓያ ሆኖ የመንቀሳቀስ ግዴታ አለበት፡፡

## 11. ከተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር የሚኖር ግንኙነት፣

ማንኛውም የፓርቲው አመራርና አባል ከሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር የሚኖረው ግንኙነትን በተመለከተ የሚከተሉትን የስነ-ምግባር ድንጋጌዎችን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

1) ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ጋር የሚደረግ ግንኙነት በትብብር እና በፉክክር መካከል ሚዛን የጠበቀ እንዲሆን የማድረግ፤
2) በሀገራችን የመግባባት ዴሞክራሲን (Consociational Democracy) ለማጎልበት እንቅፋት ከሆኑ ድርጊቶች የመቆጠብ፤
3) ተፎካካሪ ፓርቲዎች በሀገሪቱ ህጎች መሰረት የፖለቲካ ስራ የመስራት መብታቸውን የሚገድብ ድርጊት ያለመፈጸም፤
4) ፓርቲው ከሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚለይባቸውን የፕሮግራምና የፖሊሲ ጉዳዮች እንዲሁም በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚኖርን አቋም በግልጽ ተገንዝቦ ዴሞክራሲያዊ የሃሳብ ትግል በማድረግ ህብረተሰቡ ልዩነቶችን እንዲገነዘባቸው በትኩረት የመስራት፤

5) ከሌሎች ፓርቲዎች አመራሮችና አባላት ጋር የሚኖር ግንኙነት ዴሞክራሲያዊና ሰላማዊ እንዲሆን እና የሚያጋጥሙ ልዩነቶችን በውይይትና በሰለጠነ የሃሳብ ትግል ለመፍታት ጥረት የማድረግ፤
6) መርህ አልባ እና ህገ ወጥ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ህግና ሥርዓትን በጠበቀ መልኩ የመታገል ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## 12. የህግ የበላይነትን ከማስከበር አኳያ የሚኖሩ ግዴታዎች፣

ማንኛውም የፓርቲ አመራርና አባል/ላት የህግ የበላይነትን ከማስከበር አኳያ የሚከተሉትን የስነ-ምግባር ድንጋጌዎችን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

1) አንድ የብልጽግና አባልና አመራር የፍትህና ዳኝነት ተቋማት ነጻና ገለልተኛ መሆናቸውን አምኖ መቀበል አለበት፡፡
2) የፍትህና ዳኝነት ተቋማት ስራዎቻቸውን በተገቢው መልኩ እየተወጡ ስለመሆናቸው ሕገመንግስታዊ አሰራሩን በመጠበቅ ክትትልና ድጋፍ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡
3) የፍትህና ዳኝነት ተቋማት ለህብረተሰቡ ተገቢውን አገልግሎት መስጠት አለመቻላቸው ሲረጋገጥ መርህንና ሕገ መንግሰታዊ አሰራርን ብቻ መሰረት በማድረግ ተጠያቂ የሚሆኑበትን ሁኔታ የመፍጠር ኃላፊነት አለበት፡፡

## 13. የኮሙዩኒኬሽንና የሚዲያ አጠቃቀም ግዴታዎች፣

ማንኛውም የፓርቲ አመራርና አባል ከኮሙዩኒኬሽንና የሚዲያ አጠቃቀም አኳያ የሚከተሉትን የስነ ምግባር ድንጋጌዎችን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

1) የኮሙዩኒኬሽን ሥራንና የሚዲያ አጠቃቀምን በእቅድና በብቃት የመጠቀም፣ የፓርቲውን ስኬቶች ለሕዝብ የማስገንዘብና አፍራሽ ፕሮፓጋንዳን የመመከት ግዴታ አለበት፣
2) የሚዲያ ተቋማትን የመተባበርና መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት፣
3) ሚዲያ ነጻና ገለልተኛ ለህዝብ ጥቅም የተቋቋመ ተቋም መሆኑን የማክበር ግዴታ አለበት፤
4) በሚዲያ የሚተላለፍ መልዕክት በሚገለፁባቸው መድረኮች አስቀድሞ በቂ ዝግጅት አድርጎ መልዕክቶችን በጥንቃቄ የማስተላለፍ ግዴታ ይኖርበታል፤

5) በሚዲያ የሚተላለፉ መልዕክቶች የብልጽግና ፓርቲ መርሆዎች፣ እሴቶች፣ እቅዶችና አቋሞች ላይ የተመሰረቱ፣ ከሕዝቡ መልካም ባህልና እሴቶች ጋር የማይቃረኑ፣ የትስስር ትርክትን መሰረት ያደረጉና የሁሉም ኢትዮጵያዊያን የወል እውነት ለማጽናት የሚረዱ ሊሆኑ ይገባል፡፡

6) አንድ የብልጽግና አባል ወይም አመራር በሚዲያ ወጥቶ ሕዝብን ከሕዝብ የሚያጋጩ እንዲሁም በሕዝቦች መካከል ጥርጣሬ የሚያጭሩ መልዕክቶችን ማስተላለፉ ሲረጋገጥ ተጠያቂ ይደረጋል፡፡

7) ሚዲያዎችን ተጠቅሞ አንድ የብልጽግና ፓርቲ አባል ወይም አመራር የግለሰቦችን ስም በመጥቀስ ወይም አከባቢን ጠቅሶ የሚወነጅል መልዕክት ካስተላለፈ በፓርቲው ደንብና አሰራር መሰረት እንዲሁም በወንጀል ተጠያቂ ይደረጋል፡፡

8) የሚዲያ አመራሮችን ወይም ባለሙያዎችን መርህንና ተጨባጭ አፈፃፀምን ወይም ተግባርን መሰረት ባላደረገ መልኩ አለአግባብ ከሃላፊነታቸው እንዲነሱ ማድረግ፣ ማስፈራራት ወይም ዛቻ ማቅረብ ተጠያቂ ያደርጋል፡፡

9) አንድ የብልጽግና ፓርቲ አባል ወይም አመራር በማህበራዊ ሚዲያዎች እርስ በእርስ ወዳጅነት የመፍጠርና ሀሳብ የመጋራት መብት አለው፤ ከዚህ ውጪ ከፓርቲው መርሆዎች፣ እሴቶችና አሰራሮች ውጭ አሉታዊ በሆነ መልኩ ሲጠቀሙ ከተገኙ ግን ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

# ክፍል አራት

## የሥነ-ምግባር ጥሰቶች እና የእርምጃ አወሳሰድ

### 14. የሥነ-ምግባር ጥሰቶች

በዚህ መመሪያ የተጠቀሱ ሌሎች የስነምግባር ጥሰቶች እንደተጠበቁ ሆነው የሚከተሉት ጉዳዮች በብልጽግና ፓርቲ ውስጥ እንደ ሥነ-ምግባር ጥሰት ይቆጠራሉ፡፡

1) የሀገሪቱን ሕገ መንግስትና ሌሎች ህጎች እንዲሁም የመንግስት ውሳኔዎችን አለማክበር፣
2) የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ፣ የአሰራር ስርዓቶች፣ መርሆዎች፣ እሴቶች፣ አቋሞችና ውሳኔዎች አለማክበር፣
3) በፓርቲ የሚሰጡ ተልዕኮዎችንና ስምሪቶችን አለመቀበልና ግዴታዎችን አለመፈፀም፣
4) ያልተገባ ጥቅምና ክብር ለማግኘት ከሌሎች አካላት ጋር መርህ አልባ ግንኙነት መፍጠር፣
5) የውስጠ ፓርቲው ዴሞክራሲ፣ አንድነት፣ ጥራትና ጥንካሬ በሚጎዱ ድርጊቶች ላይ መሰማራት፣
6) የፓርቲውን አሰራር በጣሰ መልኩ በቡድን በመደራጀት፣ የፖለቲካ አሰላለፍን በማዛነፍና የሴራ ፖለቲካ እንቅስቃሴ በማድረግ የፓርቲውን ሕልውና አደጋ ላይ የሚጥል ተግባር መፈፀም፣
7) የአባላትን ብሔር፣ ሃይማኖት፣ ጎሳ፣ አባላት የመጡበትን ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ ወይም ሌላ ልዩነትን በማጉላት፣ በመጥላት፣ በመናቅ ወይም የነጠላ ቡድናዊ ፍላጎትን ለማሳካት በመንቀሳቀስ ወይም የጽንፈኝነትንና የአክራሪነትን አስተሳሰብንና ድርጊትን በማራመድ የአባላትን አንድነት ማላላት፣ መከፋፈል እና እርስ በርሳቸው በጥርጣሬ እንዲተያዩ ማድረግ፣
8) የፓርቲውን ሚስጢር ላልተፈቀደለት ሰው ወይም አካል ማጋራት፣
9) ፓርቲውን ማጭበርበር፣ የሃሰት ሪፖርት ማቅረብ፤ በማህበራዊ ሚዲያ የሃሰት መረጃ ማጋራት እና ማሰራጨት፣
10) በሀሰት ሀሳብ እና በሀሰት መረጃ የፓርቲዉን አመራርና አባላት መገምገም፣ መመዘን፣ እርምጃ እንዲወሰድባቸዉ ማድረግና ያለ ግብራቸዉ መልካም ስማቸዉን ለማጠልሸት መሞከር፣

11) ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ላይ መሳተፍ፤ ማገዝ፤ ማደፋፈር፤ ተባባሪ መሆን፤ ሽፋን መስጠት፣

12) ከህብረተሰቡ መልካም ባህል፣ እሴት፣ ልማድና ወግ ያፈነገጠ ድርጊት መከወን ወይም ተባባሪ ሆኖ መገኘት፣

13) ሌሎች በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ፣ በዚህ መመሪያና በሌሎች የፓርቲ የአሠራር ስርዓቶች ላይ የተቀመጡ ኃላፊነቶችንና ግዴታዎች አለመወጣት፡፡

## 15. የሥነ-ምግባር ጥሰት እርምጃ አወሳሰድ ሥነ ሥርዓት

1) በዚህ መመሪያ ላይ የተጠቀሱ ጥፋቶች የፈፀመ አባልም ሆነ አመራር እንዲታረም የሚደረገው በየደረጃው በሚፈጠሩ መድረኮችና ስልጣን በተሰጠው የፓርቲው አካል ይሆናል፡፡

2) ማንኛዉም አባል አንድ የፓርቲ አመራር ወይም አባል የሥነ-ምግባር ጥሰት መፈፀሙን ለማመን የሚያስችል በቂ ምክንያት ሲኖረው አባሉ ለተደራጀበት አካል ወይም ተጠሪ ለሆነለት አካል ወይም አባሉ በጉዳዩ ላይ ምላሽ እንዲሰጥ አባሉ በሚገመገምበት ወይም በሚመዘንበት መድረክ ላይ ሂስ ወይም መረጃና ማስረጃ ያቀርባል፡፡

3) ጥፋት ፈፅሟል የተባለው አባል በሚመለከተው አካል ተጣርቶ ወይም ተገምግሞ ቅጣት የሚያስቀጣዉ መሆኑ በአባላት አብላጫ ድምጽ ከጸደቀ በኋላ ተጠሪ ለሆነለት አካል ይቀርባል፡፡ ተጠሪ የሆነለት አካል አመራር ኮሚቴ ወይም የአስተባባሪ ኮሚቴ ካመነበት ቅጣቱ ተፈጻሚ እንዲሆን አባሉ ለተደራጀበት አደረጃጀት ወይም ውሳኔ ያሳለፈው መሰረታዊ ድርጅት ከሆነ ለአባላት በማሳወቅ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

4) በአባላትና አመራሮች ስነ ምግባር መመሪያና ተገቢ በሆኑ የፓርቲዉ መመሪያዎች መሰረት የዉሳኔዉ ተገቢነት ያልታመነበት ከሆነ ይህዉ ተብራርቶ ቅጣቱ ላይ ማሻሻያ አልያም ቅጣቱ ተፈጻሚ እንዳይሆን ይደረጋል፡፡

5) የዲስፕሊን ጥሰት ግምገማ ሃሳብ የቀረበበት አባል ግምገማዉን አስመልክቶ ምላሽ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ በግምገማና ምዘና አሰራር መሰረት ምላሹን ካዳመጠ በኋላ ስልጣን የተሰጠው አካል ዉሳኔ ያሳልፋል፡፡

6) በተገምጋሚዉ ወይም ተማዛኙ ላይ የቀረቡ የዲስፕሊን ጥሰት፤ የግምገማና ምዘና ሀሳቡም ሆነ የተገምጋሚዉ ምላሽ እንዲሁም የዉሳኔ ሀሳቡ በሚመለከተው አካል አማካኝነት በመዝገብ ላይ መስፈር ይገባዋል፡፡

7) የሚቀርብ የዲስፕሊን ክስ ተደራጅቶ ለሚወስነዉ አካል የሚቀርበዉ በየደረጃው በሚገኝ የአደረጃጀት ዘርፍ አማካኝነት ይሆናል፡፡
8) በየደረጃው በሚገኝ የአደረጃጀት ዘርፍ የዲስኘሊን ክስ አጣርቶ የውሣኔ ሀሣብ የሚያቀርብ የዲስኘሊን ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡
9) ማንኛውም አባል በሚሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ካለው በየደረጃው ለሚገኝ የፓርቲ አደረጃጀት ቅሬታ አቅርቦ በሚሰጠው ውሳኔ ካልረካ፤ በየደረጃው ለሚገኘው የኮሚሽን መዋቅር አቤቱታውን የማቅረብና መልስ የማግኘት ሙሉ መብት አለው፡፡

## 16. ተግሳፅ የሚያሰጡ ጥፋቶች

ተግሳፅ የሚያሰጡ የሥነ-ምግባር ጥፋቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1) የፓርቲውን ተልዕኮ በተሟላ መልኩ በውጤታማነት አለመፈፀም፣
2) የህዋስ ወይም የመሰረታዊ ድርጅት መደበኛ የውይይት ፕሮግራም ላይ ያለ በቂ ምክንያት ለአንድ ጊዜ አለመገኘት፣
3) በግል ማህበራዊ ድረ-ገፅ ከፍተኛ ጉዳት የማያደርሱ የተሳሳተ መረጃ ለመጀመሪያ ጊዜ ያጋራ፣
4) የፓርቲውን አባል ወይም አመራር ተገቢ ያልሆኑ ቃላትን በመጠቀም ለመጀመሪያ ጊዜ መናገር፣
5) ያለበቂ ምክንያት የአባላት ወርሃዊ ክፍያ ለአንድ ወር አለመክፈል፡፡

## 17. የቃል ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ ጥፋቶች

የቃል ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ የሥነ-ምግባር ጥፈቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1) የፓርቲውን ተልዕኮ በመፈፀም ረገድ የፍቃደኛነትና የዝግጁነት ማነስ የታየበት ከሆነ፣
2) ልዩነቶችን በውይይት ለመፍታት ከመሞከር ይልቅ ለመጀመሪያ ጊዜ ከፍተኛ ጉዳት በማያደርስ መልኩ በፀረ-ዴሞክራሲያዊ መንገድ ለመፍታት መሞከር፣
3) ከፓርቲዉ መተዳደሪያ ደንብና መመሪያ ዉጭ የአባላት ምልመላ ማከናወን፣
4) ከአንዱ አባል ወደ ሌላ አባል ከፍተኛ ጉዳት የማያደርስ አሉባልታ ለመጀመሪያ ጊዜ የመንዛት ሁኔታ የታየበት፣
5) በህዋስ ወይም በመሠረታዊ ድርጅት መደበኛ የውይይት ፕሮግራም ያለበቂ ምክንያት በተከታታይ ለሁለት ጊዜ አለመገኘት፣
6) የፓርቲ እና የመንግስት የሥራ ሰዓት ያለማክበር፣

7) በስራው ላይ ተገቢ ጥረትና ትጋት አለማሳየት፣
8) ፓርቲው በሰጠው ተልዕኮ ውጤታማ አለመሆኑ ሂስ ተደርጎ ሊታረም አለመቻል፣
9) በአገሪቱ ህግ መሰረት በወቅቱ ሀብት አለማስመዝገብ፣
10) የሐሰት ሪፖርትና የተዛባ መረጃን ሳያጣሩ ማስተላለፍ፣
11) ከስራ ባልደረቦች ጋር በመግባባት ተባብሮ መስራት ባለመቻል በስራ ሂደት ላይ እንቅፋት መሆን፣
12) ስላከናወናቸው ሥራዎች ለሚመለከተው አካል በወቅቱ ሪፖርት ያለማድረግ፣
13) ወርሃዊ የአባልነት ክፍያ ያለበቂ ምክንያት ለሁለት ተከታታይ ወራት አለመክፈል፣
14) ሌሎች ተመሳሳይ ጥፋቶችን መፈጸም፡፡

## 18. የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ ጥፋቶች

የፅሑፍ ማስጠንቀቂያ የሚያሰጡ የዲሲፕሊን ጥፋቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1) ከፓርቲው ዓላማና ፕሮግራም ጋር የሚቃረን አቋም ሆን ብሎ ለአንድ ጊዜ ማንፀባረቅ፣
2) በአባላትና በሕዝቡ መካከል ህብረ-ብሔራዊ ወንድማማችነት/እህትማማችነት እና አገራዊ አንድነት እንዳይጠናከር እንቅፋት የሚሆኑ ሐሳቦችን በይፋ ለአንድ ጊዜ ማንፀባረቅ፣
3) የፓርቲውን አባል ወይም አመራር ተገቢ ያልሆኑ ቃላትን በመጠቀም ለሁለተኛ ጊዜ ማሸማቀቅ፣
4) ፓርቲው የሚያጋጥመውን ፓለቲካዊ ፈተና በፅናት ከመጋፈጥና ከመታገል ይልቅ የወላዋይነት አቋም መያዝ፤
5) ከፓርቲ መርህ ውጭ የሆኑ ወይም የፓርቲ አቋም ያልሆኑ ጉዳዮችን ለአንድ ጊዜ በማንኛውም ሚዲያ ማሰራጨት፣
6) በፓርቲ ስራዎችና በመንግስት ስራዎች ላይ ዝቅተኛ አፈጻጸም ያስመዘገበ ወይም ለተከታታይ ሁለት የምዘና ዙሮች መካከለኛ አፈጻጸም ያስመዘገበ፣
7) ፓርቲው በመደበው ቦታ እና የሥራ ዘርፍ ያለበቂ ምክንያት ለማገልገል ፍቃደኛ አለመሆን፣
8) ከብልጽግና ፓርቲ መርህ ውጪ አዳዲስ አባላትን መደለያ በመስጠት ወይም በመቀበል ምልመላ ያደረገ፣

9) በሀሰት/በፈጠራ/ ሀሳብ እና በሀሰት መረጃ የፓርቲዉን መሪዎችና አባላት መገምገምና እርምጃ እንዲወሰድባቸዉ ማድረግና ያለ ግብራቸዉ መልካም ስማቸዉን ለማጠልሸት መሞከር፣

10) ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሲፈጸሙ እያዩ እርምት እንዲደረግ አለማድረግ ወይም አለመታገል፣

11) የህዋስ ወይም የመሰረታዊ ድርጅት መደበኛ የውይይት ፕሮግራም ላይ ያለ በቂ ምክንያት በተከታታይ ከሶስት ጊዜ በላይ አለመገኘት፣

12) ያለበቂ ምክንያት የአባልነት ወርሃዊ ክፍያ ለአራት ተከታታይ ወራት አለመክፈል፣

13) በስራ ቦታና በህንረተሰቡ ውስጥ ለሞራል፣ ለመልካም ሥነ-ምግባርና ለእሴት ተቃራኒ የሆነ ድርጊት መፈጸም፤

14) ሌሎች ተመሳሳይ ደረጃ የሚታዩ ከባድ ጥፋቶችን መፈጸም፡፡

## 19. ከኃላፊነት የሚያስነሱ የስነ-ምግባር ጥፋቶች

የፓርቲ አመራሮችን ከኃላፊነት የሚያስነሱ የዲሲፕሊን ጥፋቶች የሚከተሉት ናቸው፡፡

1) የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብ፣ እሴት፣ መመሪያ እና ውሳኔ አለማክበር፤ በዚህም በፓርቲዉ ህልዉና እና ዓላማዎች ከፍተኛ አሉታዊ ተጽእኖ መፍጠር፣

2) ከፓርቲው ዓላማና ፕሮግራም ጋር የሚቃረን አቋም በይፋ ከአንድ ጊዜ በላይ ማንፀባረቅ፣

3) ህብረ-ብሔራዊ ወንድማማችነት/እህትማማችነትን እና አገራዊ አንድነትን በከፍተኛ ደረጃ የሚጎዳ ድርጊት መፈፀም ወይም መጠነኛ ጉዳት የሚያደርሱ ድርጊቶችን በተደጋጋሚ መፈፀምና ስህተትን ለማረም ዝግጁ አለመሆን፣

4) በፓርቲው የተሰጠውን ኃላፊነትና ተልዕኮ በብቃት አለመወጣት እና በጽሁፍ ማስጠንቀቂያም ተሰጥቶት አለማስተካከል፣

5) የሕዝብን ደህንነትና የአገርን ሉዓላዊነት አደጋ ላይ የሚጥል አመለካከት መያዝ፤ ይህንኑ አመለካከት በተግባር አንፀባርቆ መገኘት፣

6) ጉቦ መቀበል ወይም እንዲሰጠው መጠየቅ፣ ሙስና መፈፀም፣ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራስ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት መስራት፣

7) በአገሪቱ ህግ መሰረት በትክክል ሀብት ለማስመዝገብ ዝግጁ አለመሆን፣

8) የቡድን መንፈስን በመጠበቅ ከሥራ ባልደረቦች ጋር ተግባብቶ ተልዕኮን ለመፈፀም አለመቻል፤ ፀረ ዲሞክራሲያዊ የሆኑ ተግባራትን በተደጋጋሚ መፈፀም፣ የፓርቲውን አባል ወይም አመራር ተገቢ ያልሆኑ ቃላትን በመጠቀም ሁለት ጊዜ በላይ ማሸማቀቅ፣

9) በፓርቲው ሕልውና ላይ አደጋ በሚጋርጥ የአንጃነትና የቡድንተኛ እንቅስቃሴ መሣተፍና የቡድንተኝነት አስተሳሰብን ማራመድ፣

10) የፓርቲን ተልዕኮና የጋራ ውሳኔዎች በጠበቀ ሁኔታ ከላይ ወደታች የሚተላለፉ ውሳኔዎችን ከመፈፀምና የሥራ አቅጣጫዎችን ከመከተል ይልቅ የግል ፍላጎትን ማዕከል አድርጎ በመንቀሳቀስ በፓርቲ ላይ ጉዳት ማስከተል፣

11) በተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች መካከል ግጭት ሊያስከትል የሚችል ወይም ሀገርንና ፓርቲውን በከፍተኛ ደረጃ የሚጎዳ መልእክት በማህበራዊ ሚዲያዎችና በመደበኛ ሚዲያዎች ማሰራጨት ወይም ማጋራት፣

12) በሀሰት/በፈጠራ/ እና በሀሰት መረጃ የፓርቲዉን አመራሮችና አባላት መገምገም፣ መመዘንና እርምጃ እንዲወሰድባቸዉ ማድረግና ያለ ግብራቸዉ መልካም ስማቸዉን ለማጠልሸት መሞከር እና እንዲያስተካክል ቢገለጽለትም ማስተካከል አለመፈለግ፣

13) አመራር እና አባላትን ለመጉዳት፣ እርምጃ ለማስወሰድ ወይም ለማጥቃት በማሰብ ሀሰት በመፍጠርም ሆነ እዉነታን በማዛባት ስልጣንን በመጠቀም አመራሮችና አባላት ላይ ማደራጀት እና መደራጀት፡፡

14) የሐሰት ሪፖርት ከአንድ ጊዜ በላይ ማስተላለፍ፣

15) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1-14 የተደነገጉት እንደተጠበቀ ሁነው የተፈፀመው የስነ ምግባር ጥፋት ከማስፈፀም አቅም ማነስ ጋር የተያያዘ ከሆነ ወይም የተፈፀመው የሥነ-ምግባር ጥፋት ከኃላፊነት ከማንሳት ይልቅ ከነበረው የኃላፊነት ደረጃ ዝቅ አድርጎ መመደብ ከጥፋቱ እንዲታረም ያስችላል ተብሎ ሲታመን ከያዘው ኃላፊነት ዝቅ ባለ ደረጃ መመደብ ይቻላል፡፡

## 20. ከኃላፊነትና ከአባልነት ስለማገድ

1) የተፈፀመውን የሥነ ምግባር ጥፋት ለማጣራት ተጨማሪ ጊዜ ሲያስፈልግና አመራሩ በኃላፊነት መቆየቱ ችግር ያስከትላል ተብሎ ሲታመንበት የመጨረሻ ውሳኔ እስከሚሰጥ ድረስ ከሦስት ወር ባልበለጠ ጊዜ የሾመው/የመደበው አካል ወይም ስልጣን የተሰጠው አካል ከኃላፊነት ታግዶ እንዲቆይ ያደርጋል፡፡

2) አንድ አባል በዚህ መመሪያ የተጠቀሱ የሥነ-ምግባር ጥፋቶች በመፈፀም ክስ የቀረበበት እንደሆነ የተደራጀበት መሰረታዊ ድርጅት ወይም ከፍ ብለው ያሉ የፓርቲው አካላት ጉዳዩን አይተው ውሳኔ እስከሚሰጡ ድረስ ከሁለት ወር ለልበለጠ ጊዜ አባሉን ከአባልነት አግደው ለማቆየት ይችላሉ፡፡

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 በተወሰነው ጊዜ ገደብ ውስጥ ተፈጽሟል የተባለውን የዲስፕሊን ጥፋት አጣርቶ ለውሳኔ ማብቃት ያልተቻለ እንደሆነ ለተጨማሪ አስራ አምስት (15) የስራ ቀናት ብቻ ማራዘም ይቻላል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የታገደው አመራር ከኃላፊነቱ ሲታገድ በተከሰሰበት ጉዳይ ውሳኔ እስኪሰጠው ድረስ የመንግስትና የፓር ተቋማት አሰራርን በጠበቀ መልኩ ያለው ደመወዙ ሊከፈለው ይችላል፡፡

## 21. ከአባልነት የሚያሰርዙ የሥነ-ምግባር ግድፈቶች፡-

የሚከተሉት ጥፋቶች ከአባልነት ሊያሰርዙ የሚችሉ ከባድ የዲሲፕሊን ጥፋቶች ናቸው፡፡

1) ሕብረ ብሔራዊ ወንድማማችነትንና አገራዊ አንድነትን በተመለከተ ፓርቲው ከያዘው አቋም የተለየ አቋም ማራመድና ይህንኑ በተግባር መግለፅ፣

2) የሃሰት ሪፖርት ማቅረብ፤ ፓርቲውን ለማጭበርበር መሞከር፣ ሃሰተኛ መረጃዎችንና መግለጫዎችን በማህበራዊ ሚዲያ እና ሌሎች ሚዲያዎች ማሰራጨት፣

3) ከፓርቲ የተሰጠን ኃላፊነት የግል ጥቅም ማካበቻ ማድረግ፤ በሙስናና ብልሹ አሰራር ውስጥ መገኘት፤ በራስ ወይም በሌላ አባል ላይ የተጀመረን የዲሲፕሊን ክስ ምርመራን ለማደናቀፍ መሞከር፣

4) የፓርቲውን ሕልውና አደጋ ውስጥ ለመጣል በአንጃኝነትና በቡድንተኝነት መንቀሳቀስ፤

5) ብሔርን፣ ሃይማኖትን፣ የኑሮ ደረጃን ወይም ሌላ ማህበራዊ መለያን መሠረት በማድረግ የፓርቲ አባላት የአስተሳሰብና የተግባር አንድነት እንዳይኖራቸው እና እንዲከፋፈሉ ማድረግ፣

6) በየእርከኑ ወይም በየደረጃው በሚገኘው የፓርቲ መዋቅር የሚደረጉ ስብሰባዎች ምልዓተ ጉባኤ እንዳይሟላ በማሰብ ሆነ ብሎ በተደጋጋሚ ከስብሰባ መቅረትና ሌሎች እንዳይገኙ ማድረግ፣

7) ፈተናዎችን በፅናት ከመጋፈጥ ይልቅ ማምለጫ መንገዶችን ለግል ጥቅሙ ብቻ በማሰብ መንቀሳቀስ፣

8) መርህ አልባ በሆነ መንገድ የተወሰኑ አካላትን ድጋፍ ለማግኘትና በህዝበኛነት በሕዝቦች መካከል ጥርጣሬና ግጭት ሊፈጥር የሚችል ስሜት ኮርኳሪ ንግግር ማድረግ ወይም በማህበራዊ ሚዲያ አልያም በማንኛዉም ሚዲያ ማጋራት፣

9) ፓርቲው በሚያስተላልፋቸው ውሳኔዎች ላይ በግል የተያዙ አቋሞችን የቡድን ወይም አጠቃላይ የፓርቲው አቋም አድርጎ ማቅረብና ማሰራጨት፣

10) የሌላ የፖለቲካ ፓርቲ አባል ሆኖ መገኘት፣

11) በፍርድ ቤት በሚሰጥ ውሳኔ የመደራጀት /ሲቪልና የፖለቲካ መብቱ/ መገፈፍ፣

12) የፓርቲውን ድረ ገፆች፣ የዜና አውታሮች እና ልዩ ልዩ ሚዲያዎችን በመጠቀም ፓርቲው በሕዝቡ ዘንድ ተአማኒነትና ተቀባይነት እንዳይኖረው መስራት፣

13) ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ አለመሆኑ ሲረጋገጥ፣

14) በቂ ባልሆነ ምክንያት ወርሃዊ የአባልነት ክፍያን ለስድስት ተከታታይ ወራት አለመክፈል፣

15) ሰርጎ ገብ ሆኖ በፓርቲ አባልነት ሽፋን ልዩ ተልዕኮ ይዞ መንቀሳቀስና የሌላ አካል ዓላማ አስፈፃሚ መሆን፡፡

## 22. ከአባልነት የተሰናበተ አባል ተመልሶ አባል የሚደረግበት ሁኔታ

1) ከአባልነት የተሰናበተ ሰው ውሳኔው ከተላለፈ ከአንድ አመት በኃላ በጥፋቱ መጸጸቱንና መሻሻል ማሳየቱን ገልፆ ወደ አባልነት ለመመለስ በጽሑፍ የዲስፕሊን እርምጃ ለወሰደበት አካል ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2) የዳግም አባል ልሁን ጥያቄ ሊቀርብ የሚገባዉ በዲስፕሊን እርምጃ ተወስዶበት ከአባልነት ተሰናብቶ በነበረዉ ግለሰብ በራሱ ሲሆን የመመለስ ጥያቄዉን በጥፋቱ መጸጸቱንና የጸባይና የተግባር መሻሻል ስለማድረጉ የሚያሳምኑ መረጃዎችን በማከል ማቅረብ ይኖርበታል፣

3) የዳግም አባልነት ጥያቄ የቀረበለት ቀድሞ ውሳኔ ያስተላለፈ አካል አጣርቶ በ ¾ ድምጽ ያፀደቀ እንደሆነ የውሳኔ ሐሳቡን አንድ ደረጃ ከፍ ላለ የፓርቲው አካል ያቀርባል፣

4) ከዚያም የውሳኔ ሐሳብ የቀረበለት አካል የውሳኔ ሐሳቡን ከመረመረ በኀላ አግባብነት ያለው ሆኖ ካገኘው የዳግም አባልነት ጥያቄውን በ3/4 ድምጽ ያጸድቃል፣

5) ቀድሞ የዲስፕሊን ቅጣት ያስተላለፈበት መዋቅር ጋር በስራም ሆነ በመኖሪያ አካባቢ እንደማይገናኝ ከተረጋገጠ አሁን በሚሰራበት/በሚኖርበት አካባቢ ባለች መሰረታዊ ድርጅት ጥያቄዉን ሊያቀርብ ይችላል፣
6) የዳግም አባልነት ጥያቄዉ የቀረበለት መዋቅር ቀድሞ ከአባልነት ያሰናበተዉ መዋቅር ሳይሆን ግለሰቡ አሁን በስራ/በመኖሪያ ቀይሮ የመጣበት መዋቅር በሚሆንበት ጊዜ ቀድሞ ከአባልነት የመሰናበት ዉሳኔ ካስተላለፈበት መዋቅር ላይ የዉሳኔዎችን ዶክመንቶች ኮፒ በመቀበል ለቀረበለት ጥያቄ ምርመራ እንደዋና መነሻ አድርጎ መጠቀም ይኖርበታል፣
7) የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ቢኖርም አንድን አመራር ወይም አባል በምንም መልኩ ከአንድ ዓመት በታች መመለስ ፈጽሞ የተከለከለ ነው፡፡

## 23. ቅጣትን የሚያከብዱ ሁኔታዎች

1) ክስ የቀረበበትን ጥፋት በተደጋጋሚ መፈፀም፣
2) በጥፋት አለመፀፀትና ይህንኑ በተግባር ለመግለፅ አለመቻል፡፡

## 24. ቅጣትን የሚያቀሉ ሁኔታዎች

1) አባሉ ወይም አመራሩ የፈፀመው ጥፋት በፓርቲው፣ በሀገርና በሕዝብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የማያደርስ ከሆነ የዲሲፕሊን እርምጃ ውሳኔ በሚወሰንበት ወቅት የሚከተሉት ጉዳዮች እንደ ቅጣት ማቅለያ ከግምት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ፡፡
   ሀ) ጥፋትን ማመን፣ መፀፀትና ይህንኑ በተግባር መግለፅ፣
   ለ) ክስ ከቀረበበት ጉዳይ ውጭ መልካም ሥነ-ምግባር ያለው ለመሆኑ በሌሎች አባላት የሚሰጥ ምስክርነት፣
   ሐ) በተሰማራበት መስክ መልካም የሥራ አፈፃፀም የነበረው መሆኑ፣
   መ) ጥፋት የፈፀመው ለመጀመሪያ ጊዜ መሆን እና
   ሠ) ለማህበረሰቡ ከፍ ያለ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የፈፀመ መሆን፡፡

# ክፍል አምስት

## የቅሬታና አቤቱታ አቀራረብና አፈታት የአሰራር ስርዓት

### 25. የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

1. ማንኛውም የፓርቲው አመራር ወይም አባል ከፓርቲው መተዳደርያ ደንብና መመሪያዎች ውጭ አድሎ ተፈጸመብኝ ብሎ ካመነ ቅሬታውን ከህዋስ ጀምሮ እስከ ፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ድረስ ማቅረብ ይችላል፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በየደረጃው የሚቀረብው ቅሬታ ከታችኛው የፓርቲ አካል ውሳኔ የተሰጠው ጉዳይ ቀጥሎ ላለው አካል መቅረብ ይኖርበታል፣
3. በየደረጃው የሚቀርበው ቅሬታ በፅሁፍ ሆኖ የቅሬታ አቅራቢው ሙሉ ስም፣ የቅሬታ ጭብጥ፣ ደጋፊ ማስረጃዎች፣ ውሳኔ የተሰጠው እንደሆነ ከውሳኔው ጋር በፊርማ ተደግፎ መቅረብ ይኖርበታል፣
4. ማንኛውም ቅሬታ አቅራቢ ለቅሬታው መነሻ የሆነ ውሳኔ ወይም ድርጊት ከተፈፀመበት ጊዜ አንስቶ ባሉት ተከታታይ ቀናት፡-
   ሀ) ለመሠረታዊ ድርጅት በአንድ ወር ውስጥ፣
   ለ) የቀበሌ /መሰረታዊ ድርጅት/ ከወሰነበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ውስጥ ለወረዳ ወይም በወረዳ ደረጃ ላሉ ከተሞች ጽ/ቤት፣
   ሐ) የወረዳ ቅርንጫፍ ብልጽግና ጽ/ቤት ከወሰነበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ውስጥ ለዞን ወይም በዞን ደረጃ ላሉ ከተሞችና ክፍለ ከተሞች ጽ/ቤት፣
   መ) የዞን ቅርንጫፍ ብልጽግና ጽ/ቤት ከወሰነበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ውስጥ ለክልል ብልጽግና ጽ/ቤት እና
   ሠ) የክልል ቅርንጫፍ ብልጽግና ጽ/ቤት ከወሰነበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ውስጥ ለማዕከል ብልጽግና ዋና ጽ/ቤት ካልቀረበ በይርጋ የታገደ ይሆናል፣
5. ቅሬታ የቀረበለት የፓርቲ መዋቅር ቅሬታው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ምላሹን በጽሑፍ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

### 26. ለኮሚሽኑ የአቤቱታ አቀራረብ ሥርዓት

1. ማንኛውም የፓርቲው አባላት ከፓርቲው መተዳደርያ ደንብና መመሪያዎች ውጭ ርምጃ ተወስዶብኛል ወይም አድልኦ ተፈጽሞኛል ብሎ ካመነ አቤቱታውን በየደረጃው ላለው ኮሚሽን ማቅረብ ይችላል፣

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የሚቀርበው አቤቱታ በየደረጃው ላለው የፓርቲ መዋቅር አቅርቦ በውሳኔው ካልረካ ብቻ ይሆናል፣
3. በየደረጃው ለኮሚሽኑ የሚቀርበው አቤቱታ በፅሁፍ ሆኖ የአቤቱታ አቅራቢው ሙሉ ስም፣ የአቤቱታ ጭብጥ፣ የውሳኔ ግልባጭ እና ሌሎች ደጋፊ ማስረጃዎች ጋር በፊርማ ተደግፎ መቅረብ ይኖርበታል፣
4. ማንኛውም አቤቱታ አቅራቢ የሚመለከተው አካል ለአቤቱታው መነሻ የሆነ ውሳኔ ከሰጠበት ጊዜ አንስቶ ባሉት ተከታታይ ሶስት ወራት ውስጥ ማቅረብ ይኖርበታል፣ በሶስት ወር ውስጥ ካልቀረበ አቤቱታ በይርጋ የታገደ ይሆናል፡፡

## 27. የሥነ-ምግባር ክስ፣ የውሳኔ አሰጣጥና ቅሬታ አቀራረብ

1) የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት የሥነ-ምግባር ክስ፣ የውሳኔ አሰጣጥና የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡
   ሀ) የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል የዲሲፕሊን ጥፋት ክስ የሚታየው በማዕከላዊ ኮሚቴው ነው፡፡ ክሱ ለማዕከላዊ ኮሚቴ የሚቀርበውም በፓርቲው ዋና ጽ/ቤት አማካይነት ይሆናል፡፡
   ለ) ማዕከላዊ ኮሚቴው የቀረበለትን ክስ በዚህ መመሪያ መሠረት ከመረመረ በኋላ የራሱን ውሳኔ ያሳርፍበትና ለጉባኤው ያቀርባል፡፡
   ሐ) ጉባኤው በማዕከላዊ ኮሚቴ የቀረበለትን የውሳኔ ሃሳብ ሊያፀድቅ ወይም ሊሽር ይችላል፡፡ የጉባኤው ውሳኔ ይግባኝ የማይባልበት የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል፡፡
   መ) ክስ የቀረበበት የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ማዕከላዊ ኮሚቴው ለጉባኤው በሚያቀርበው የውሳኔ ሃሳብ ላይ ቅሬታ ካለው ለጉባኤዉ ከመቅረቡ አስቀድሞ ቅሬታውን ለኢንስፔክሽንና ሥነ-ምግባር ኮሚሽን ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ኮሚሽኑ የማዕከላዊ ኮሚቴውን የውሳኔ ሃሳብ የሻረው እንደሆነ የውሳኔ ሃሳቡ ውድቅ ይሆናል፤ ለጉባኤም አይቀርብም፡፡
   ሠ) ማዕከላዊ ኮሚቴው ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ በኮሚሽኑ ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ እንደሆነ ጉባኤው ተከሳሹ በአካል ተገኝቶ ሃሳቡን እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡ ጉባኤው ተከሳሹን ካዳመጠ በኋላ ውይይት አድርጎ ይግባኝ የማይጠየቅበት የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

2) የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ያልሆኑ አባላትና አመራሮች የስነ ምግባር ክስ፣ ዉሳኔ አሰጣጥና የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

ሀ) የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ያልሆኑ አመራሮችና አባላት የዲሲፕሊን ጥፋት ክስ የሚቀርበው አባል በሆነበት መዋቅር ወይም አባሉን በቅርበት የመከታተል ኃላፊነት ያለበት አመራር ወይም እውነተኛ መረጃና ማስረጃ ባለው ማንኛውም አባልና አመራር ሊሆን ይችላል፡፡

ለ) በአመራር ወይም አባል ላይ የቀረበው ክስ የሚታየው አባሉ በታቀፈበት የፓርቲ አደረጃጀት ይሆናል፡፡

ሐ) በዚህ መመሪያ መሠረት በአደረጃጀቱ በተሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው አመራር ወይም አባል ለትዩዩ ኢንስፔክሽንና ስነ ምግባር ኮሚሽን ቅሬታዉን ማቅረብ ይችላል፡፡

ለ) በአቤቱታ በቀረበለት የኢንስፔክሽንና ስነ ምግባር ኮሚሽን ምላሽ ያልተስማማ አመራር ወይም አባል አቤቱታውን አንድ እርከን ከፍ ላለ የኮሚሽኑ አካል አቤቱታውን ሊያቀርብ ይችላል፡፡

ሐ) ማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ላልሆኑ አባላትና አመራሮች በወረዳ ደረጃ ላሉት እና በይግባኝ ከቀበሌ/መሰረታዊ ድርጅት ለቀረበ አቤቱታ የወረዳ ኢንስፔክሽንና ሥነ-ምግባር ኮሚሽን፣ በዞን ደረጃ ላሉት እና በይግባኝ ከወረዳ ለቀረበ የዞን ኢንስፔክሽንና ሥነ-ምግባር ኮሚሽን፣ በክልል ደረጃ ላሉት እና በይግባኝ ከዞን ለቀረበ የክልል ኢንስፔክሽንና ሥነ-ምግባር ኮሚሽን እና በፌዴራል ደረጃ ላሉት እና በይግባኝ ከክልል ለቀረበ የማዕከል የኢንስፔክሽንና ሥነ-ምግባር ኮሚሽን የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ውሳኔ ይሆናል፡፡

3) የኢንስፔክሽንና ሥነ-ምግባር አመራርና አባላትን በተመለከተ

1) የኢንስፔክሽንና ስነ ምግባር ኮሚሽን አመራርና አባላት መመሪያ ቁጥር1/2014 በጸደቀው የኮሚሽኑ የአሰራርና አደረጃጀት መመሪያ ላይ በተቀመጠው የአሰራር ስርዓት መሰረት ተጠያቂ እንዲሆኑ የሚደረግ ይሆናል፡፡

## 28. የቅሬታ ወይም አቤቱታ የማጣራት ሥርዓት

1. የቀረቡትን ቅሬታዎች ወይም አቤቱታዎች ቅቡልነት እና በበቂ መረጃ የተደገፈ ስለመሆኑ ይጣራል፣ ያልተሟላ መረጃ ካለ እንዲሟላ መደረግ ይኖርበታል፣
2. ቅሬታ የቀረበለት የፓርቲ አካላት አጣሪ ኮሚቴ አዋቅሮ ቢበዛ በአንድ ወር ውስጥ ማጣራት ይኖርባቸዋል፣
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ቅሬታ ለማጣራት የተቋቋመ የኮሚቴ አባላት የፓርቲውን መተዳደሪያ ደንብና መመሪያዎች መሰረት በማድረግ በገለልተኝነት ማጣራት ይኖርባቸዋል፣
4. በየደረጃው ለኮሚሽኑ የቀረቡ የአባላት አቤቱታ ከኮሚሽኑ አመራሮች ወይም አባላት ወይም በኮሚሽን ጽ/ቤት ሠራተኞች ተሰይመው ቢበዛ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ መጣራት ይኖርበታል፣
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) የተጣራ አቤቱታ ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ለኮሚሽኑ መቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 29. የውሳኔ አሰጣጥ ሥርዓት

1. ከአባላት የሚቀርቡ ቅሬታዎች በአጣሪ ኮሚቴ ተጣርተው በየደረጃው ለሚገኙ የፓርቲ አመራር አካላት ቀርበው በዚህ መመሪያ መሰረት ውሳኔ መሰጠት ይኖርባቸዋል፣
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የውሳኔ ሃሳብ የቀረበለት የፓርቲ የአመራር ኮሚቴ ተጨማሪ ማጣራት ወይም አስረጂ አስቀርበው ማጣራት ይችላሉ፣
3. በየደረጃው ውሳኔ የሰጠው የፓርቲ አመራር አካል ውሳኔውን ለሚመለከታቸው የፓርቲ አካላት ሲልኩ፣ ለቅሬታ አቅራቢው የውሳኔውን ግልባጭ በጽሁፍ መስጠት ይኖርባቸዋል፣
4. በቀረበው ቅሬታ ላይ የተሰጠው ውሳኔ ቢበዛ በሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ለሚመለከታቸውና ለቅሬታ አቅራቢው እንዲያውቁት መደረግ ይኖርበታል፣
5. አቤቱታ ቀርቦለት ያጣራ ወይም የመረመረ በየደረጃው የሚገኝ የኮሚሽኑ አካል ውሳኔውን ከእርምት የውሳኔ ሐሳብ ጋር እንደአግባቢነቱ በየደረጃው ላሉ የፓርቲ አስተባባሪ ኮሚቴ ወይም አካላት በጽሁፍ መስጠት ይኖርባቸዋል፣
6. የኮሚሽኑ የእርምት የውሳኔ ሐሳብ ተቀባይነት ካላገኘ በመተዳደሪያ ደንቡ አንቀጽ 23(10) መሠረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

7. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የኮሚሽኑ ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

## 30. የውሳኔ አሰጣጥ ይዘት

1) የቀረቡት የቅሬታ ወይም አቤቱታ ጭብጦች፣ የቀረቡ የውሳኔ ሐሳቦችና የተሰጡ ውሳኔዎች፣
2) የፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ እና መመሪያዎች ድንጋጌዎች፣
3) ውሳኔው በየደረጃው በአካል የተወሰነ ስለመሆኑና ውሳኔውን በሰጡ አባላት መካከል ልዩነት ካለ የልዩነት ነጥብ የተገለጸ ስለመሆኑ እና
4) ውሳኔው ላይ የተገኙ አባላት የፈረሙበት ቃላ ጉባዔ መሆን ይኖርበታል፡፡።

## 31. የቅጣት ውሳኔ ስለማሳወቅ

1) ማንኛውም አባል የተወሰደበትን የሥነ መግባር እርምጃ ወይም የቅጣት ውሳኔ በጽሑፍ የማግኘት መብት አለው፣
2) የፓርቲው ዋና ጽ/ቤት በፓርቲው የተወሰደውን የሥነ ምግባር እርምጃ ወይም የቅጣት ውሳኔ ለተወሰደበት የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡
3) በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲ ጽ/ቤቶች በፓርቲው የተወሰደውን የሥነ ምግባር እርምጃ ወይም የቅጣት ውሳኔ ለተወሰደበት አመራር ወይም አባል በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡
4) የፓርቲ ጽ/ቤቶች ለሥነ ምግባር እርምጃ ወይም ለቅጣት ውሳኔ መነሻ የሆኑ የግምገማና ምዘና ሰነዶችን በተጠየቁ ጊዜ የማሳየት ግዴታ አለባቸው፡፡

# ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 32. የአመራርና የአባላት ስንብት ስለማጸደቅ

በዚህ መመሪያ መሠረት የአባላት ስንብት አባሉ በተደራጀበት የፓርቲው አካል ውሳኔ ሐሳብ አቅራቢነት በመሠረታዊ ድርጅት ጠቅላላ አባላት ኮንፈረንስ ቀርቦ መፅደቅ አለበት፡፡

### 33. የተወሰዱ የዲስፕሊን እርምጃዎች ስለመመዝገብ

በየደረጃዉ የሚገኙ የፓርቲው ጽ/ቤቶች የሥነ-ምግባር እርምጃ የተወሰደባቸውን አመራሮችና አባላትን ዝርዝር መረጃ እና የግምገማና ምዘና መረጃዎችን ሰንዶ በሀርድ ኮፒ የመያዝ እና እንደአግባብነቱ በዳታ ቤዝ የማደራጀትና የመያዝ ግዴታ አለባቸው፣

### 34. ግንዛቤ ስለመፍጠር

ኮሚሽኑ እና በየደረጃው የሚገኙ የፓርቲው መዋቅሮች መመሪያውን በሚመለከት ለአመራርና ለአባላት ግንዛቤ ለማዳበር ስለመመሪያው ዓላማ፣ ይዘት እና አፈጻጸም በተለያየ ደረጃና ስልት ተከታታይነት ያለው የማስተዋወቅ፣ የመረጃ ስርጭትና ግንዛቤ የማስጨበጥ ስራ ይሰራሉ፡፡

### 35. የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም የፓርቲ አካላት፣ አመራርና አባላት ይህን መመሪያ የማክበር፣ የማስከበርና ለተፈጻሚነቱ የመተባበር ግዴታ አለባቸው፡፡

### 36. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው አሰራሮች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ልማዳዊ አሰራሮች ወይም መመሪያዎች በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

### 37. መመሪያውን ስለማሻሻል፣

ይህን መመሪያ ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በፓርቲው ማዕከላዊ ኮሚቴ ሊያሻሽል ይችላል፡፡

## 38. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በማዕከላዊ ኮሚቴ ከጸደቀበት --------------- ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ፣ ------- ቀን 2015 ዓ.ም.**

**የብልፅግና ፓርቲ ማዕከላዊ ኮሚቴ**